# የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ
ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ



የቅጂ መብት © 2024 GSM Association

# ሞጁል 12፡- ተንቀሳቃሽ ገንዘብ

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

## ይህ ምንድን ነው?

ዝርዝሩ ክፍት መሆኑን በማረጋገጥ፣ ቁልፍ ተግባራትን የሚያሳይ የተንቀሳቃሽ ገንዘብ አገልግሎት ያለው መደበኛ ተንቀሳቃሽ ስልክን ያሳዩ።

**ያብራሩ፦** «ተንቀሳቃሽ ገንዘብ ስልክዎን በመጠቀም ለሌላ ሰው ገንዘብ መላኪያ መንገድ ነው።»

## የሚያስፈልጉዎ ቁሳቁሶች፦



ተንቀሳቃሽ ስልክ




የተንቀሳቃሽ ገንዘብ ፖስተሮች

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ያብራሩ፦**

«የተንቀሳቃሽ ገንዘብ መለያ ማለት የኪስ ቦርሳዎን በስልክዎ እንደመያዝ ማለት ነው። በተንቀሳቃሽ ገንዘብ፣ የባንክ መለያ ሳይኖርዎ ለሰዎች ገንዘብ መላክ እና መቀበል እና ስልክዎን ብቻ በመጠቀም ክፍያዎችን መፈጸም ይችላሉ! በተንቀሳቃሽ ገንዘብ አቅራቢዎ ላይ የሚመሰረት ሆኖ፣ በተጨማሪም የአገልግሎት ክፍያዎችንና የትምህርት ቤት ክፍያዎችን መክፈል፣ በርቀት ሆነው ዕቃዎችን መግዛት እና ገንዘብ ማስቀመጥ ወይም መበደር የመሳሰሉ ብዙ ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ።»

ስለ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ ጥቅሞች እና በግልዎ እንዴት እንደሚጠቀሙበት የራስዎን ምሳሌዎች ለሰልጣኙ **ያጋሩ**።

## ለምን ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

**ለሰልጣኙ ሕይወት እንዴት** ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል በመወያየት ከሰልጣኙ ጋር የሚገናኝ እንዲሆን ያድርጉት። ለሚከተሉት የሰልጣኝ ዓይነቶች ተገቢ የሆኑ ምሳሌዎችን ታሳቢ ያድርጉ፦

**አዛውንት፦** ርቆ ለሚኖር ቤተሰብ ገንዘብ ይላኩ ወይም ከእነሱ ይቀበሉ ወይም እንደ መብራት የመሰሉ የአገልግሎት ክፍያዎችን መጓዝ ሳይጠበቅብዎ ከቤትዎ ሆነው ይክፈሉ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ጥሬ ገንዘብ በማስቀመጥ ወይም በመያዝ የሚኖረውን የደህንነት ስጋት ይቀንሱ።

**እናት ወይም የቤት እመቤት፦** የትምህርት ቤት ክፍያዎችን ካሉበት ሆነው ይክፈሉ፤ ለወደፊት የቤተሰብ ፍላጎቶች ወይም እንቅስቃሴዎች የበለጠ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ገንዘብ ያስቀምጡ፤ ለቤተሰብ ፍላጎቶችዎ ብድር ያግኙ፤ ርቆ ከሚኖር ሰው በቀላሉ ገንዘብ ይቀበሉ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ጥሬ ገንዘብ በመያዝ የሚፈጠርን የደህንነት ስጋት ይቀንሱ።

**የንግድ ባለቤት፦** ጥሬ ገንዘብ መያዝ ሳያስፈልግዎ ለአቅራቢዎች ወይም ለሰራተኞች ይክፈሉ እንዲሁም ከደንበኞች በቀላሉ ክፍያዎችን ይቀበሉ፤ ለንግድዎ ብድር ያግኙ።

**ገበሬ ወይም የገጠር ሰው፦** ለግብርና ግብዓቶች ክፍያ ይፈጽሙ ወይም ለምርቶች ከሩቅ ቦታ ክፍያዎችን ይቀበሉ፤ ከገዢዎች ጋር ሲገናኙ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በመያዝ የሚፈጠርን የደህንነት ስጋት ይቀንሱ።

**ወጣት፦** በርቀት ሆነው የዩኒቨርሲቲ ክፍያዎችን ይክፈሉ ወይም ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን ይግዙ፤ በቁጠባዎ ላይ ወለድ ያግኙ።

# እንዴት ነው የሚሰራው?

## ስልኩን በሰልጣኙ እጅ ላይ ያድርጉት እና ቅደም ተከተሎችን እንዲከተሉ ያግዟቸው።



**«ስልክዎን በመጠቀም ለጓደኛ ገንዘብ መላክ» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

በፖስተሩ ላይ ያሉትን ቅደም ተከተል በመጠቀም ሰልጣኙ እንዴት ለጓደኛ ገንዘብ መላክ እንደሚችሉ **ያሳዩ**።

«አሁን ስልክዎን ተጠቅመው እንዴት ለጓደኛ ገንዘብ መላክ እንደሚችሉ አሳይዎታለሁ።»

«በትክክል መለያዎን ተጠቅመው ገንዘብ ለመላክ ከፈለጉ፣ ይህን ማድረግ እንችላለን። ወይም በተንቀሳቃሽ ገንዘብ መለያዎ ውስጥ ገንዘብ ከሌለዎት ወይም አሁን መላክ የማይፈልጉ ከሆነ፣ ለወደፊቱ እንዲያውቁ እንዴት እንደሚሠራ ማሳየት እችላለሁ።»

- የስልክ አገልግሎት አቅራቢዎ የተንቀሳቃሽ ገንዘብ አገልግሎታቸውን ለመጠቀም አጭር ቁጥር ይኖራቸዋል። እንደ *123# ዓይነት ነው። ይጻፉት እና የመደወያ አዝራሩን ይጫኑ።
- በማያ ገጹ ላይ የአማራጮች ዝርዝር ያገኛሉ (ለምሳሌ፣ 1፣2፣3፣4፣5)። ገንዘብ ማስተላለፍ/መላክን መምረጥ አለብዎት። ይህ በተለምዶ ቁጥር 1 (ከላይ) ነው። በስልክዎ የቁልፍ ሰሌዳ ላይ 1ን ይጫኑ ከዚያ እሺ የሚለውን ይጫኑ ወይም ይምረጡ።
- ገንዘቡን ሊልኩላቸው የሚፈልጉት ጓደኛዎን ወይም የቤተሰብዎ አባልን ስልክ ቁጥር ይጻፉ። ምረጥ/እሺን ይጫኑ።
- አሁን ለጓደኛዎ ወይም ለቤተሰብዎ አባል ለመላክ የሚፈልጉትን የገንዘብ መጠን (ለምሳሌ፣ 100) ይጻፉ። ምረጥ/እሺን ይጫኑ።
- የግልዎን ሚስጥር ቁጥር ይጻፉ። ይህ እርስዎ የመረጡት የተለየ ቁጥር እና እርስዎ ብቻ የሚያውቁት ነው። ይህ መለያዎን ለመጠበቅ ያግዛል። ለመገመት የሚከብድ ሚስጥር ቁጥር ይምረጡ። ምረጥ/እሺን ይጫኑ።
- በመጨረሻም፣ ይህን ገንዘብ ለመላክ መፈለግዎን ለማረጋገጥ 1ን መጫን ይኖርብዎታል። ምረጥ/እሺን ይጫኑ። እንኳን ደስ አለዎት። ለጓደኛዎ ወይም ለቤተሰብዎ አባል ገንዘብ ልከዋል።

**ጠቃሚ ምክር፦**
በስልጠናው መጀመሪያ ላይ አስቀድሞ የተንቀሳቃሽ ገንዘብ መለያ ያለው ማን እንደሆነ ያረጋግጡ። የተንቀሳቃሽ ገንዘብ መለያ የሌላቸው ሰልጣኞች ካሉ፣ የምዝገባ ሂደቱን አከናውኑላቸ (ለዝርዝሮች «ጥልቅ» ክፍለ-ጊዜን ይመልከቱ)።

**ጠቃሚ ምክር፦** ሰልጣኙ ምንም ገንዘብ መላክ ካልፈለጉ፣ እንዴት እንደሚሰራ ገንዘቡ የእውነት ሳይላክ ያሳዩዋቸው።

## ልምምድ ያድርጉ!

**«አሁን ተንቀሳቃሽ ገንዘብን በመጠቀም ገንዘብ እንዴት መላክ እንደሚቻል ተመልክተናል፣ ለማን ገንዘብ ሊልኩ ይችላሉ?»**

**አሰልጣኝ፦** ሰልጣኙ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ሌላ ሰው የመላክ ሂደቱን እንዲያከናውኑ ይፍቀዱ። በየትኛውም ደረጃ ላይ እገዛ ቢያስፈልጋቸው ይርዷቸው።

## ደህንነት



**«በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች» የሚለውን ፖስተር ያሳዩ።**

«የእርስዎ ሚስጥር ቁጥር የግልዎ ቁጥር መሆኑን ያስታውሱ። ወደ መለያዎ የሚገቡበት መንገድ ስለሆነ ይህን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መያዝዎ አስፈላጊ ነው። ይህን ቁጥር ለማንም ሰው፣ ለተንቀሳቃሽ ገንዘብ ወኪሎች ወይም ለደንበኞች እንክብካቤ ሠራተኞች ቢሆንም እንኳን፣ በአካል፣ በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ወይም በበይነመረብ አማካኝነት እንዳያጋሩ ጥንቃቄ ያድርጉ።»

«ለማያውቁት ወይም ለማያምኑት ሰው ወይም በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው በፍጹም ገንዘብ አይላኩ። ሰዎች ገንዘብ እንዲልኩላቸው ለመጠየቅ ሊያነጋግሩዎት ይችላሉ። አጭበርባሪ ሊሆኑ ስለሚችሉ ገንዘብ አይላኩላቸው።»

# ፖስተሮች እና ተቆርጠው የወጡ ማሳያዎች

## የስልክ በይነመረብ ክህሎቶች የሥልጠና መርጃ ስብስብ

ሰዎችን መደበኛ የስልክ በይነመረብ ክህሎቶችን ለማስተማር የተዘጋጀ መመሪያ

# በመስመር ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ ምርጥ ጠቃሚ ምክሮች

**በይነመረብ በዓለም ዙሪያ ላሉ ሰዎች ሁሉ ክፍት መሆኑን ያስታውሱ፣ ስለዚህ እንደ እውነተኛው የህዝብ መገናኛ ቦታ (ለምሳሌ፣ የገበያ ቦታ) ማየቱ አስፈላጊ ነው እንዲሁም ራስዎን በመጠበቅ እና በመስመር ላይ ለሚያደርጉት ነገር ኃላፊነት በመውሰድ ደህንነትዎን ይጠብቁ።**

## በመስመር ላይ የሚመለከቱት ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ያስታውሱ

ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ነገር በመስመር ላይ መለጠፍ ይችላል፣ ስለዚህ የሚመለከቱትን ሁሉ አይመኑ። ከሚያምኑት ሰው እንኳን ቢሆን እውነት ላይሆን ይችላል። መረጃን ለሌሎች ከማጋራትዎ በፊት ጥንቃቄ ያድርጉ።

## በመስመር ላይ ለተዋወቁት ሰው ገንዘብ ከመላክዎ በፊት ደግመው ያስቡ

ያልጠየቋቸውን ኢሜይሎች፣ መልዕክቶች ወይም ብቅ-ባዮች በተለይም ገንዘብ የሚጠይቁ ከሆኑ ወይም እንግዳ የሆኑ አገናኞችን ከያዙ ይጠንቀቋቸው።

## የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ የግል መረጃዎን ለግልዎ ያቆዩ

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር፣ እንደ ሙሉ ስምዎ፣ የቤት አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ያሉ የግል ዝርዝሮች ማጋራት የለብዎትም።

## በመስመር ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት አያድርሱ

መልካምነትን እና አክብሮትን ያሳዩ። ጉልበተኝነት አያሳዩ፣ የውሸት መረጃን አያሰራጩ ወይም ማንም ሰው ላይ ትንኮሳ አያድርሱ። በመስመር ላይ የሚወስዷቸው እርምጃዎች በእውነተኛ ሕይወት ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

## ማጭበርበሮችን እና አጭበርባሪዎችን ይወቁ

ልክ በእውነተኛ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ በበይነመረብ ላይም ሌቦች እና ወንጀለኞች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በመስመር ላይ ሌላ ሰው እንደሆኑ ያስመስላሉ።

## የሚያስቸግርዎትን ሰው በማገድ ወይም ችላ በማለት እርምጃ ይውሰዱ

የሆነ ሰው በመስመር ላይ ካስቸገረዎ ወይም ትንኮሳ ካደረሰብዎ፣ እርዳታ ይጠይቁ እንዲሁም ለሆነ ሰው ይናገሩ ወይም ሪፖርት ያድርጉ።

# የዳታ ወጪዎች



## ተንቀሳቃሽ ገንዘብ

# ስልክዎን በመጠቀም ለጓደኛ ገንዘብ መላክ



ተንቀሳቃሽ ገንዘብ

# ስልክዎን በመጠቀም ሂሳብ መክፈል



# ተንቀሳቃሽ ገንዘብ ምንድን ነው?



የኪስ ቦርሳዎን በስልክዎ
እንደማለት ነው።



በወኪልዎ ከተንቀሳቃሽ ገንዘብ
መለያዎ ጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ
ሊደረግ እና ወጪ ሊሆን ይችላል።



ለሌሎች ሰዎች ገንዘብ መላክ፣
ሂሳቦችን መክፈል፣ ለዕቃዎች
መክፈል ይችላሉ።



የሚስጥር ቁጥርዎ መለያዎን
የሚጠቀሙበት መንገድ ነው።

ተንቀሳቃሽ ገንዘብ

# ለተንቀሳቃሽ ገንዘብ መለያ መመዝገብ



ከስልክ አገልግሎት አቅራቢዎ
ሲም ካርድ ያስፈልግዎታል።
የተንቀሳቃሽ ገንዘብ ወኪልዎ
ለተንቀሳቃሽ ገንዘብ
ይመዘግቡዎታል።



ለተንቀሳቃሽ ገንዘብ
ለመመዝገብ የማንነት
ማረጋገጫ ያስፈልግዎታል።



ወደ መለያዎ ገንዘብ
ለማስቀመጥ ወይም ከመለያዎ
ገንዘብ ለማውጣት በሚፈልጉበት
ጊዜ ሁሉ ወደ ወኪልዎ ይሂዱ።



እነዚህ ቅደም ተከተሎች
ከተጠናቀቁ በኋላ የተንቀሳቃሽ
ገንዘብ መለያዎን መጠቀም
መጀመር ይችላሉ!

ተንቀሳቃሽ ገንዘብ

# በተንቀሳቃሽ ገንዘብ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ

ለጓደኞች ወይም
ቤተሰቦች ገንዘብ ይላኩ

ከጓደኞች ወይም
ቤተሰብ ገንዘብ ይቀበሉ

ሂሳቦችን ወይም የትምህርት
ቤት ክፍያዎችን ይክፈሉ

ለእርስዎ ወይም ለሌሎች
ሰዎች የአየር ሰዓት ይግዙ

በሌሎች አገሮች ውስጥ ለሚኖሩ
ጓደኞችዎ እና ቤተሰብዎችዎ
ገንዘብ ይላኩ / ከእነሱ ይቀበሉ

ለዕቃዎች እና
አገልግሎቶች ይክፈሉ

በቁጠባዎችዎ
ላይ ወለድ ያግኙ

ብድር ያግኙ

ተንቀሳቃሽ ገንዘብ

# ተንቀሳቃሽ ገንዘብን ሲጠቀሙ ደህንነትን ጠብቆ መቆየት



መልዕክት



ሚስጥር ቁጥር



ስልክ



ወኪሎች

